# እንዲህ ነዋ!*

ከውጭ፣ ከውርጭ ቤት ሲገቡ
            ሙቅቱ፣ ስሜቱ
እንዴት ነው ቢሉሽ - ትርንጎውን
ትንፋሽሽ በሮማን ከንፈርሽ -
እፍፍፍ... በዪባቸው
አትፍሪ፣ አትፈርያቸው
"እንዲህ ነዋ!"      በያቸው።



የዓጋሙ፣ የቀጋው፣ የኢደሱ፣ የጥሪኝ
            መዓዛው፣ ሽታው
እንዴት ነው ቢሉሽ - ጋሜሽን
ግለጭው፣ ሽሩባሽን
ፍቺው... አሳዪአቸው...
አትፍሪ፣ አትፈርያቸው
"እንዲህ ነዋ!"      በያቸው።



ጨረቃ ብቅ ስትል ከዳመና ውስጥ
            ብርሃንዋ፣ ድምቀትዋ
እንዴት ነው ቢሉሽ - መቀነትሽን
ፍቺው፣ አውልቂው ልብስሽን...
አሳዪአቸው...
አትፍሪ፣ አትፈርያቸው
"እንዲህ ነዋ!"      በያቸው።



የሱስ ሙታንን ያስነሳው
            በረቂቁ  ታምር
እንዴት ነው ቢሉሽ - ጠጋ  በዪኝና
ከንፈሬ ላይ ሳሚኝ - ፍቅርሽን
አሳዪአቸው...
አትፍሪ፣ አትፈርያቸው
"እንዲህ ነዋ!"      በያቸው።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

* ዝከረ ሩሚ